# የዲፕሎማቱ ... (4)

(ዘነበ ኃይለማርያም)

የክፍል 3 መጨረሻ ከጅቡቲ የወደብ ድንበር ኢሚግሬሽን ኦፊሰሮች ጋር መገናኘቴን፣ በወያኔ የስለላ ሰዎች እጅ የመውደቁ ስጋት መቀጠሉን ገልጩ ነበር ያቆምኩት:: በመቀጠል በጅቡቲ የነበረኝን አጭር ነገር ግን አስጨናቂ ቆይታ ስገልጽላችሁ ካስተዋልኩትና ከተገነዘብኩት አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳ ነው:: በነገራችን ላይ እስከ ዛሬ በተከታተላችሁት እውነተኛ ታሪክ ለማስተላለፍ የተፈለገው ቁምነገር በጠባብ ጎሰኞች (የትግራዩ አንጃ) በአገራችን እየተፈጸመ ያለውን የሰብዓዊ መብት መደፈር፣ ንጹሃን ዜጎችን ማሰር እና ማሰቃየት፣ የዜጎች በሀገራቸው ስራ የማግኘት መብትን የመንፈግ፣ ዜጎች ከሀገራቸው እንዲፈናቀሉ ማድረግን፣ የአስተሳሰብና ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትን የመንፈግ፣ ባለሙያና ምሁራን በሀገራቸው ባይተዋር እንዲሆኑና በሙሉ አቅማቸው ለሀገር አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት እንዳይችሉ ማነቆ የሆነ አምባገነን ስርዓት ሀገራችንን ወደ ጥልቅ የድህነት አዘቅት እየከተታት መሆኑን በማጋለጥ የዜግነት ግዴታዬን ለመወጣትና ይህን የብሔር ወገንተኝነት ደዌ የተጠናወተውን ስርዓት በግልጽ በተቻለኝ ሁሉ ለመታገል ነው::

ከዋናው ርዕሠ ጉዳዬ ልውጣና ለራሳችሁ የምትመልሱት አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ:: በኢትዮጵያ ባለው ጠባብ የጎሳ አገዛዝ ስር የሚኖር ሰው የህይወት፣ የንብረትና የሥራ ዋስትና ምን ያህል ነው? ምላሹ ምን እንደሚሆን ልቦናችሁ ያውቃል:: የትግራዩ አንጃ በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርሰውን በደል ስናስብ ሊያስማሙን የሚችሉ እውነታዎች አሉ:: መቼም ስርዓቱ ለ18 ዓመታት ስልጣን ላይ መፈናጠጡን እንኳን እናንተ ባለቤቱም አይክድም:: ይህ አንጃ በዚህ የአንድ ትውልድ ቆይታው በየጊዜው "ጥቂት" እያለ የገደላቸው፣ አካለጎዶሎ ያደረጋቸው፣ በዘብ ጥያ (እስር ቤት) አስገብቶ ያሰቃያቸው፣ ዛሬ በእስር ቤት ከርችሞ የሚያሰቃያቸው፣ ደብዛቸውን ያጠፋቸው፣ ከሥራ ገበታቸው አፈናቅሎ ቤተሰቦቻቸው እንዲበተኑ ያደረጋቸው እና በአጠቃላይ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች የተፈጸመባቸው እጅግ ብዙ ናቸው:: ዓለም ጠግቦ እያደረ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚላስ የሚቀመስ አላጣም የሚል ይኖራል ብዬ በፍጹም አልገምትም:: ይሄ ሁሉ ሲሆን ታዲያ ምን ይሆን የምንጠብቀው?

የኢትዮጵያ ታሪክ የነፃነት ተጋድሎን የሚተርክ ቢሆንም ዛሬ ግን ሁላችን በአንጃው ስንረገጥ፣ ስንጨፈለቅ እና በገዛ ሀገራችን ባይተዋር ሆነን መቀጠላችን ለምን ይሆን? አንጃው ለራሱ ታገለና "ታጋይ" የሚል ስያሜ ለራሱ ሰጠ:: "ከእኔ ወዲያ ላሳር" ማለት ከጀመረ ዓመታት ተቆጥሯል:: ይቅርታ አድርጉልኝና ኢትዮጵያዊ ሆነን ለክፋት ጠባብ ጎሰኞችና የጥቅም ተገዮች እውቀታችንንና

ጉልበታችንን ሸቀጥነው፡፡ ክቡር ኢትዮጵያዊነታችንን ሆን ብለው ካሳነሱት ከእነዚህ ጎሰኞች ጋር ተባብረን አጎደፍነው፡፡ በዲሞክራሲ ስም አምባገነንነትን የሚያስፋፋ፣ በልማት ስም ጥፋትን የሚያደራጁ፣ በሰላም ስም ብጥብጥና አለመረጋጋትን የሚጠነስሱ እኩዮችን ተመልክተን ዳተኛ በመሆናችን የታሪክ ተወቃሾች እንሆናለን፡፡ እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ምናልባት የበቃ እውቀትና ልምድ ያላችሁ በርካቶች ስለምትኖሩ ለእናንተ በመተው ወደ ጅቡቲ ልመልሳችሁ፡፡

የጅቡቲ የወደብ ፖሊሶች ከኢሚግሬሽን ኃላፊ አገናኙኝ፡፡ በርካታ ጥያቄዎችን ካቀረበልኝ በኋላ እንድገባ ፈቀደልኝ፡፡ በየጎረቤት ሀገሮች በሀገራቸው መቆሚያና መቀመጫ አጥተው፣ ረሃብንና ችግርን ሸሽተው፣ ለህይወታቸውና ለደህንነታቸው ሰግተው ዙሪያው ገደል የሆነባቸውን ዜጎች ለማደንና ኑሯቸውን የሰቀቀን ለማድረግ በውጭ ምንዛሪ(በአሜሪካን ዶላር) ከፍተኛ ክፍያ የሚከፈላቸው የወያኔ ካድሬዎች(ራሳቸውን እንደሚጠሩት ታጋይ) ክትትል ለመሰወር ከዚህ በፊት በአካል በማላውቃት ጅቡቲ ሸርጥ፣ ኮፍያ እና ስካርቭ አድርጌ ወደ ማህበረሰቡ ተቀላቀልኩ፡፡ በወያኔ እጅ ከገባው አረመኔያዊና ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች እንደሚፈጸሙብኝ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነበርኩ፤ ነገር ግን አንድ የማውቀው እውነታ አለ፡፡ የወያኔ የደህንነት ክፍል እንደ ውጭ ጉዳዩና ኤምባሲው የአንድ ብሄር ጥርቅሞችና ጥቂት ጭሎዎች ስብስብ ሲሆን፣ ያላቸው ንቃተ ህሊና ዝቅተኛ ነው፡፡ ቢሆኑም ጥንቃቄ ማድረግ ስለነበረብኝ ቢሰባበርም እናገር የነበረው አረብኛ ቋንቋ ነበር፡፡ አንድ የጅቡቲና የየመን ተወላጅ የሆነ የጅቡቲ ዜጋን በሽፋንነት ተጠቅሜ አገሪቱን ከመልቀቁ በፊት መጀመሪያ አንድ ግለሰብ ትኩረቴን በሳበ ጤናማ ባልሆነ አስተያየት እየተመላለሰ ተመለከተኝ የነበርኩበት ቦታ ወደ ኬንያ ሊያስወጣኝ የሚችል ወሳኝ ስፍራ ስለነበር መሸሽ አልፈለኩም፡፡

በመቀጠል ግለሰቡ ከስፍራው ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከእይታዬ ከተሰወረ በኋላ ከአንድ ሌላ ግለሰብ ጋር መጣ፡፡ በዚህ ወቅት ሳልሸበር ቀደም ሲል ካፈራሁት ሽፋን ጋር ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ በአረብኛ እያወራን የተወሰኑ ርቀቶችን ጠብቄ ተጠጋኋቸው፡፡ በትግሬኛ ነበር የሚነጋገሩት፡፡ መጀመሪያ ሲመለከተኝ የነበረው ግለሰብ ቀጠን ብሎ ትንሽ ረዘም ያለ ነው፡፡ ሌላኛው መካከለኛ ቁመት ሲኖረው ወፍራም ባይባልም ሰውነቱ ደህና ነው፡፡ ይህ ግለሰብ የመጀመሪያውን ባለበት በመተው በግምት 20 ሜትር በሚሆን ርቀት ላይ ቆሞ ግራ ቀኙን ያማትር ጀመር፡፡ ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላም አንድ ጅንስ ሱሪ ያደረገች ከአንገቷ ጎበጥ ያለች ሴት እና ቁምጣ ካደረገ አንድ ግለሰብ ጋር ተጨባበጡ፡፡ ምን እንደሚያወሩ ባይገባኝም እያንዳንዷን እንቅስቃሴያቸውን በጥሞና አስተውል ነበር፡፡ ተራ በተራ ይመለከቱኝ ነበር፡፡ ራሳቸው ናቸው ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ከሰነዓ በመኪና አቆራርጬ በኋላም በባህር ከወጣሁ በኋላ ወዲያውኑ መኖሪያ ቤቴ በኤምባሲው እንዲታሽግ ተደርጓል፡፡ ለየመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤትና ለየመን የደህንነት ክፍል ፈልገን ስላጣነው የት እንደተሸሸገ ግለጹልን ወይም ደግሞ ከየመን ከወጣ

ግለሰቡ የያዘው ፓስፖርት ዋጋ የሌለው ነው እያልናችሁ በምን ዓይነት መንገድ ሊወጣ እንደቻለ ይገለጽልኝ ሲል ኤምባሲው ጠይቋል:: ስለዚህ ልደርስ የምችልበትን ርቀትን ገምተው በኤምባሲው የሚገኙት የወያኔ ደህንነቶችና ወታደሮች በየአካባቢው ለሚገኙት መሰሎቻቸው ነግረዋቸዋል::

መቼስ በእጃቸው አለመውደቁ የአምላኬ ታምር ነው እንጂ ጥበበኛ ሆኜ አይደለም:: በዚህ ዛሬም አሳዳጆቼ በቁጭት ይብሰለሰላሉ:: አብሬአቸው እያለው ዛቻው፣ማስፈራራቱና ስድቡ የእለት ተለት ተግባራቸው ነበር:: እናንተዬ ለካስ "ሥር የሰደደ አባዜ በቀላሉ አይለቅም" የሚባለው እውነት ኖሯል:: መቼም ምን ተፈጠረ እንደማትሉኝ እምነቴ ነው:: ለማንኛውም በዚሁ ድህረ- ገጽ የመን የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ባወጣው "ጋዜጣዊ መግለጫ" ሳትደመሙ አልቀራችሁም:: እኽ ብላችሁ ካዳመጣችኋቸው እነዚህ ሀገር እንመራለን፣ እናስተዳድራለን የሚሉ የትግራይ አንጃዎችና ጭሎዎች የማይሉት የለም:: ለማንኛውም ኤምባሲው ጋዜጣዊ መግለጫ በሚል ርዕስ የደረደራቸውን ቃላቶች አስመልክቶ ያለኝን አመለካከት ከመግለጽ አልቆጠብም::



© COPYRIGHT 2002-2009: Ethiomedia.com. All rights reserved. Ethiomedia.com, a premier African American news and views portal, , disclaims endorsement of the different views reflected here.